# በጨው ግብይት መመሪያ ቁጥር 962/2015 (ማሻሻያ) ረቂቅ መመሪያ ላይ የቀረበ አጭር መግለጫ

## 1. የማሻሻያ መመሪያው አስፈላጊነት

በጨዉ ምርት ግብይት ላይ የሚስተዋሉትን የተለያዩ ችግሮች በመቅረፍ ህብረተሰቡ በአዮዲን የበለጸገና ጥራቱን የጠበቀ ጨው ለፍጆታ ማግኘት እንዲችል፣ ጨውን በግብአትነት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች በቂ ግብዓት ማግኘት እንዲችሉ እና በዘርፉ ፍትሐዊ የንግድ ውድድር እንዲኖር በማድረግ በአጠቃላይ ሀገሪቱ ከዘርፉ ተገቢዉን የኢኮኖሚ ጥቅም ማግኘት እንድትችል የጨው ግብይትን ለመቆጣጠር የሚያስችል መመሪያ ቁጥር 962/2015 ወጥቶ ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ከዘርፉ ተዋንያን እና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚቀርቡ ቅሬታዎች ዘርፉ የጸረ ንግድ ውድድር ተግባራት የሚስተዋሉበት፣ በጥቂት ነጋዴዎች በሞኖፖል የተያዘ እና ጨውን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች በቂ ግብአት ለማግኘት መቸገራቸውን በመግለጽ ተደጋጋሚ ቅሬታዎች የቀረቡ በመሆኑ ምክንያት በጨው ምርት፣ ግብይትና ስርጭት ዙሪያ አጭር የዳሰሳ ጥናት ማድረግ ያስፈለገ ሲሆን ጥናቱም የሚከተሉትን ግኝቶች ጠቁሟል፡፡

የጥሬ ጨው አምራች ማህበራት በዘርፉ ውስጥ ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ያሉ እንደመሆኑ አሰራራቸውን በህግና በመመሪያ መቆጣጠር የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት የሚያስፈልግ መሆኑ፤

በጨው ግብይት መመሪያ በአንቀጽ 2(3) ላይ የጨው አቀነባባሪ ፋብሪካ የሚለው ጥሬ ጨው በሚመረትበት አካባቢ ብቻ መገኘት እንዳለበት አስገዳጅ ሁኔታዎችን የፈጠረ እና በሌሎች አካባቢዎች የሚገኙ አቀነባባሪዎች በግብአትነት የሚጠቀሙበት ጨው እንዳያገኙ የሚያደርግ፣ የንግድ ውድድርን የሚገድብ፣ የጨው ማቀነባበርና በአዮዲን የማበልጸግ ስራ በጥቂት ፋብሪካዎች እንዲያዝ የሚያደርግ እና ወደ ዘርፉ ለሚገቡ አዳዲስ ኢንቨስተሮች ሁኔታዎችን የሚያከብድ መሆኑ፤

ለቆዳ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆን ጥሬ ጨው በናፍታሊን ኬሚካል ተለውሶ እንዲወጣ ቢደነገግም መመሪያው ተግባራዊ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ ኬሚካሉን በሀገር ውስጥ ማግኘት ባለመቻሉና ከውጭ ለማስገባት ከፍ ያለ የውጭ ምንዛሪ የሚጠይቅ በመሆኑ ፋብሪካዎች የማምረት ሥራቸውን ለማከናወን መቸገራቸውን ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ በማረጋገጡና ለናፍታሊን ኬሚካል ጉዳይ መ[illegible] ማስፈለጉ፤

Ministry of Trade and Regional Integration

በተጨማሪም በገበያ ላይ የጨው እጥረት እንዳይፈጠርና ሸማቾች ለዋጋ ንረት እንዳይዳረጉ ታስቦ የጨው አቅራቢዎች የመጠባበቂያ ምርት እንዲይዙ የሚፈቅዱ ድንጋጌዎችን ላልተፈለገ ዓላማ በመጠቀም ጨውን ለማከማቸት የተጠቀሙበት መሆኑ በመመሪያው የአፈጻጸም ሂደት የታየ መሆኑ፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መሠረት በመመሪያው የአፈጻጸም ሂደት ካጋጠሙ ክፍተቶች፣ ውስንነቶችና ማነቆዎች በመነሳት ጨው በጠፈጥሮ ከሚገኝበት አካባቢ ውጪ ያሉ የጨው ፋብሪካዎች በግብዓትነት የሚጠቀሙበት ጥሬ ጨው የሚያገኙበትን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር፣ በናፍታሊን ኬሚካል እጥረት ምክንያት ለተፈጠረው ችግር መፍትሄ ለመስጠት፣ የምርት ማከማቸትን ለመከላከል እና በአጠቃላይ በዘርፉ ፍትሐዊ የንግድ ውድድር እንዲኖር ለማድረግ በሥራ ላይ ያለውን የጨው ግብይት መመሪያ ቁጥር 962/2015ን ማሻሻል አስፈልጓል።

ማሻሻያው የሚፈታቸው ቁልፍ ጉዳዮች

•ሁሉም አቀነባባሪ ፋብሪካዎች ለግብዓት የሚውል ጥሬ ጨው እንዲያገኙ የሚያስችል መሆኑ፤

•ፍትሐዊ የንግድ ውድድር እንዲኖር የሚያስችል መሆኑ፤

•በሀገር ውስጥ ለተፈጠረው የናፍታሊን ኬሚካል እጥረት መፍትሄ የሚሰጥ መሆኑ፣

•የጨው ምርት ማከማቸትን ለመከላከል የሚያስችል መሆኑ፤

•የጨው ግብይት ሥርዓትን ለማዘመን ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥር መሆኑ ናቸው።

## 2. <u>የረቂቅ መመሪያው ይዘት</u>

ረቂቅ መመሪያው በአጠቃላይ ሦስት አንቀጾችን ያካተተ ነው። በአንቀጽ አንድ የደንቡ አጭር ርዕስ የጨው ግብይት መመሪያ ቁጥር 962/2015ን ለማሻሻል የወጣ መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን አንቀጽ 2 የተደረጉትን ማሻሻያዎች በዝርዝር የሚያስቀምጥ ነው። የመጨረሻው አንቀጽ ሦስት ደግሞ መመሪያው የሚጸናበትን ጊዜ ያመለክታል።

የረቂቅ መመሪያው የማሻሻያ አንቀጽ 13 ማሻሻያዎችን ያካተተ ሲሆን በአጠቃላይ ሲታይ በ3 ጉዳዮች ዙሪያ የተደረገ ነው።

የመጀመሪያው የጨው አቀነባባሪ ፋብሪካዎች ጥሬ ጨው በሚመረትበት አካባቢ ብቻ ፋብሪካቸውን አቋቁመው እንዲሠሩ አስገዳጅ ሁኔታዎችን የፈጠረ እና በሌሎች አካባቢዎች የሚገኙትን ኢንዱስትሪዎች የሚገድብ፣ የንግድ ውድድርን የሚገድብ፣ የጨው ማቀነባበርና

2

በአዮዲን የማበልጸግ ስራ በተወሰኑ ፋብሪካዎች እንዲያዝ የሚያደርግ እና ወደ ዘርፉ ለሚገቡ አዳዲስ ኢንቨስተሮች ሁኔታዎችን የሚያከብድ መሆኑ በአፈጻጸም ሂደት የተገኘው ተሞክሮ በማሳየቱ ይህን ሁኔታ ለመለወጥና ለሁሉም ባለሀብቶች እኩል ለመወዳደር የሚያስችል የንግድ ከባቢ ለመፍጠር ያለመ ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ለቆዳ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆነው ጥሬ ጨው ከጥሬ ጨው ማምረቻ ቦታ በናፍታሊን ኬሚካል ተለውሶ እንዲወጣ የሚያስገድዱ ድንጋጌዎች ከመመሪያው እንዲወጡ በማድረግ ጥሬጨውን በግብአትነት ለሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የተደረጉ ማሻሻያዎች ናቸው፡፡

በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ በገበያ ላይ የጨው እጥረት እንዳይፈጠርና ሸማቾች ለዋጋ ንረት እንዳይዳረጉ በማሰብ የጨው አቅራቢዎች የመጠባበቂያ ምርት እንዲይዙ የሚፈቅዱ ድንጋጌዎችን ላልተፈለገ ዓላማ በመጠቀም ጨውን ለማከማቸት የተጠቀሙባቸው በመሆኑ ክምችትን የተመለከቱ ድንጋጌዎች እንዲሻሻሉ ተደርጓል፡፡

በመጨረሻም የተደረጉ ማሻሻያዎችን ተከትሎ ዋና አንቀጾችን እና ንዑሳን አንቀጾችን የሚያሸጋሽጉ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡

## 3. የመመሪያዉ የዝግጅት ሂደት፤

- ✓ ለዚህ መመሪያ ዝግጅት መነሻው በ2015 ዓ.ም በወጣው የጨው ግብይት መመሪያ ቁጥር 962/2015 አፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገር ውስጥ ንግድና የሸማቾች ጥበቃ መሪ ሥራ አስፈጻሚ እና የሕግ አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ የሥራ ክፍሎች ረቂቅ መመሪያውን አዘጋጅተው ለዘርፉ የበላይ አመራር በማቅረብ በተሰጡ ግብአቶች እንዲዳብር ከተደረገ በኋላ ለሚኒስቴሩ ሚኒ ካቢኔ ውይይት ቀርቦ ተጨማሪ ግብአት በማሰባሰብ ረቂቁን የማዳበር ሥራ ተከናውኗል፡፡
- ✓ በመቀጠልም ረቂቁ ለፍትህ ሚኒስቴር ተልኮ አስተያየት የተሰጠበት ሲሆን በተሰጡት አስተያየቶች መሠረት እንዲስተካከልና እንዲዳብር ተደርጓል፡፡ የፍትህ ሚኒስቴር ከሰጣቸው አስተያየቶች መካከል በመሠረታዊነት የተነሳው ረቂቁ ለባለድርሻ አካላት ቀርቦ ውይይት እንዲደረግበት የሚል በመሆኑ በዚሁ መሠረት ህዳር 6 ቀን 2017 ዓ.ም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል እና የክልል መንግሥት ተቋማት፣ በተለይም የጨው ምርት ከሚካሄድበት ከአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ኃላፊዎች፣ ከጨው አምራቾች፣ አቀነባባሪዎች እና ጨውን እንደ ግብአት ከሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ጋር በሚኒስቴር መ/ቤቱ የንግድ አዳራሽ በረቂቅ መመሪያው ላይ ውይይት የተካሄደ ሲሆን



የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry of Trade and Regional Integration

ሁሉም ተሳታፊዎች የመመሪያው መሻሻል በሥራ ላይ ባለው መመሪያ የተፈጠሩትን ማነቆዎች የሚፈታ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ (በምክክር መድረኩ የተያዘው ቃለጉባኤ እና የተሳታፊዎች ዝርዝር አባሪ ተደርጓል፡፡)

## 4. <u>ማጠቃለያ</u>

- ✓ የጨው ግብይትን የተሳለጠ ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ ቁጥር 962/2015 የወጣ ቢሆንም በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች በመኖራቸው እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ረቂቅ የማሻሻያ መመሪያ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡
- ✓ ረቂቅ መመሪያው በቀን 02/01/2017 ዓ/ም በቁጥር 01.1.36/70194 በተጻፈ ደብዳቤ ለፍትህ ሚኒስቴር ተልኮ ሚኒስቴሩም በ29/01/2017 ዓ.ም በቁጥር ፍሚ/9163 በተጻፈ ሸኚ ደብዳቤ አስተያየት የሰጠበት ሲሆን በረቂቁ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት እንዲደረግበት የተሰጠውን መሠረታዊ አስተያየት ጨምሮ የተሰጡ ሁሉም አስተያየቶች ተወስደው አስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጓል፡፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጡ አስተያየቶች የተስተናገዱበትን ሁኔታ በተመለከተ ራሱን የቻለ ተጨማሪ ማብራሪያ ተዘጋጅቶ አባሪ ተደርጓል፡፡
- ✓ ስለሆነም በዚህ ማብራሪያ ከዚህ በላይ በዝርዝር የቀረቡትን እና የፍትህ ሚኒስቴር የሰጣቸው አስተያየቶች የተስተናገዱበትን ሁኔታ በተመለከተ በተዘጋጀው ተጨማሪ ማብራሪያ የቀረቡትን ሀሳቦች፣ አስተያየቶች እና የጋራ መግባባቶች ታሳቢ በማድረግ መመሪያው የጸደቀ በመሆኑ በአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1283/2012 መሠረት እንዲመዘገብልን በአክብሮት አቅርበናል፡፡



CamScanner

**መመሪያ ቁጥር 1032/2017**

**የጨው ግብይትን ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ (ማሻሻያ) ቁጥር 1032/2017**

የጨው አቀነባባሪ ፋብሪካዎች ጥሬ ጨው በሚመረትበት አካባቢ ብቻ እንዲሠሩ መደረጉ የንግድ ውድድርን የሚገድብ ሆኖ በመገኘቱ፤

ለናፍታሊን ግዢ የሚያስፈልገው የውጭ ምንዛሪ የጨው አቀነባባሪ ፋብሪካዎችን ለከፍተኛ ወጪ የሚዳርግና በግብይቱ ላይ ችግር የሚፈጥር ሆኖ በመገኘቱ፤

በጨው ግብይት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ነጋዴዎች ምርቱን አላግባብ በማከማቸት በገበያ ውስጥ ሰው ሰራሽ እጥረት እንዳይፈጥሩ መከላከል በማስፈለጉ፤

እነዚህን ዓላማዎች ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ በሥራ ላይ ያለውን የጨው ግብይት መመሪያ ቁጥር 962/2015 ለማሻሻል የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ22 (1) (ለ) እና19(4) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "**የጨው ግብይትን ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ (ማሻሻያ) መመሪያ ቁጥር** 1032/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ማሻሻያ

የጨው ግብይት መመሪያ ቁጥር 962/2015 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1. አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ(3) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) ተተክቷል፦

"3. "የጨው አቀነባባሪ ፋብሪካ" ማለት በሀገሪቱ በማንኛውም ስፍራ የሚገኝ ሆኖ፦

ሀ) ጥሬ ጨውን በማጠብ እና በአዮዲን በማበልጸግ አዮዲን ያለበት መሆኑን በሚገልጽ እስከ 50 ኪሎ ግራም በሚይዝ ማሸጊያ በቀጥታ ለሰው ምግብነት ወይም ለምግብ አምራች ኢንዱስትሪዎች በጅምላ የሚያቀርብ፤ ወይም

ለ) ጥሬ ጨውን በማጠብ ጨዉ የታጠበ እና አዮዲን የሌለው መሆኑን በሚገልጽ እስከ 50 ኪሎ ግራም በሚይዝ ማሸጊያ ለግብዓትነት ለሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች በጅምላ የሚያቀርብ፤ ወይም

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር Ministry of Trade and Regional Integration



CamScanner

(ለ) ከውጪ ሀገር የሚገባውን የሚተካ ወይም ለውጪ ገበያ የሚውል የገበታ ጨው የሚያቀርብ ነው፤"

2. አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (5) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (5) ተተክቷል፡-

"5. "ጅምላ አከፋፋይ" ማለት የጨው ምርትን ከጨው አቀነባባሪ ፋብሪካዎች በመግዛት ለአነስተኛ የጨው አቀነባባሪዎች ወይም ለቸርቻሪዎች የሚያከፋፍል ነጋዴ ነው፤"

3. አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (10) ተሰርዞ ንዑስ አንቀጽ (11) ንዑስ አንቀጽ (10) ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

"10. "የምግብ ኢንዱስትሪ ግብዓት ጨው" ማለት በአዮዲን የበለጸገ ሆኖ ጨውን እንደ ግብአት ለሚጠቀሙ የምግብ አምራች ፋብሪካዎች የሚቀርብ ጨው ነው፤"

4. አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (12) ንዑስ አንቀጽ (11) ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

"11. "የኢንዱስትሪ ግብዓት ጨው" ማለት ያልታጠበ እና አዮዲን የሌለው ሆኖ ለምግብነት የማይውሉ ምርቶችን ለማምረት የሚያገለግል ለምግብነት የማይውል መሆኑን በሚገልጽ ማሸጊያ የሚቀርብ ጨው ነው፤"

5. አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ (13) ንዑስ አንቀጽ (12) ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

"12. "የጨው ምርት መግለጫ" ማለት ሌሎች ዝርዝር መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው የታጠበ፣ በአዮዲን የበለጸገ ወይም ለኢንዱስትሪ ግብአት የሚውል ጨው ስለመሆኑ በማሸጊያው ላይ የሚጻፍ መግለጫ ነው፤"

6. የመመሪያው አንቀጽ 2 ከንዑስ አንቀጽ (14) እስከ ንዑስ አንቀጽ (19) የነበሩት እንደቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀጽ (13) እስከ ንዑስ አንቀጽ (18) ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

7. በአንቀጽ 4 ስር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (8) ተጨምሮ የቀድሞው ንዑስ አንቀጽ (8) ንዑስ አንቀጽ (9) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡-



CamScanner

"8. ዘመናዊ የጨው ግብይት ሥርዓት ይዘረጋል፤"

8. አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (3) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) ተተክቷል፦

"3. ከማምረቻ ቦታ የሚወጣ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውል ያልታጠበም ሆነ የታጠበ ጨው ለምግብነት እንደማይውል በሚገልጽ ማሸጊያ እየታሸገ መውጣቱን ይቆጣጠራል::"

9. የመመሪያው አንቀጽ 7 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 7 ተተክቷል፦

" 7. የጥሬ ጨው አምራች ግዴታ

ጥሬ ጨው አምራች ጥሬ ጨውን በወቅቱ እና በጥራት በማምረት የገበያ ትስስር ለተፈጠረላቸው የጨው አቀነባባሪ ፋብሪካዎች እና ለምግብነት የማይውል መሆኑን በሚገልጽ ማሸጊያ አሽጎ በግብዓትነት ለሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች በጅምላ ያቀርባል::"

10. አንቀጽ 8 እና አንቀጽ 9 ተሰርዘው ከአንቀጽ 10 እስከ 19 የነበሩት እንደ ቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ 8 እስከ አንቀጽ 17 ሆነው ተሸጋሽገዋል::

11. አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (3) የነበረው አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (3) ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

"3. በጅምላ አከፋፋዮች አማካይነት ለምግብ ኢንዱስትሪዎች እና ለአነስተኛ የጨው አቀነባባሪዎች በአዮዲን የበለጸገ ጨው በማሸግ ለገበያ ያቀርባል፤"

12. አንቀጽ 8 ሆኖ የተሸጋሸገው አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (7) ተሰርዟል::

13. አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (3) አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (3) ሆኖ ተሸጋሽጎ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

"3. በገበያ ውስጥ የጨው እጥረት እንዳያጋጥምና የተረጋጋ የጨው ግብይት እንዲኖር አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል::"



CamScanner

3. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት እና በሚንስቴሩ ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር 24 ቀን 2017 ዓ.ም**

**ካሳሁን ጎፌ ባለሚ (ፒ.ኤች.ዲ)**

**የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር**



CamScanner